# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 39 ሚያዝያ 15/2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገፆች


በአገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት የአገልግሎት አሰራር ሥርዓት ግልጽነት ላይ በተደረገ ጥናት ውይይት ተካሄደ

ገጽ 3

የቱሪዝም ዘርፉን ከሙስና ለመጠበቅ ቴክኖሎጂንና ሥነ-ምግባርን በማቀናጀት የሀገርን ገጽታ መገንባት ይገባል - ክቡር እንደገና አበበ (ፒ.ኤች.ዲ)

ገጽ 6

ሥነ-ምግባራዊ የቢዝነስ ውሳኔ ሰጪነት ለባንክ የፋይናንስ አፈፃፀም ቁልፍ ድርሻ አለው

ገጽ 7


**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!**

## ሌብነት ሀገር አያሳድግም!



"ኢትዮጵያ በልጽጋ፣ ከችግርና ከልመና ወጥታ በዓለም መድረክ ከፍ ብላ የምትታይበትን ጊዜ ለማየት ሁላችንም በጋራ መሥራት አለብን። ሌብነት ሀገርን አያሳድግም፤ ውጤት የሚመጣው በልፋትና በንጹህ ልቦና በመሥራት ብቻ ነው።" ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

## UNCAC SECOND CYCLE PEER REVIEW — PUBLIC UPDATE





We are pleased to share an important milestone in our country's ongoing commitment to transparency, accountability, and integrity through the United Nations Convention against Corruption (UNCAC) Implementation Review Mechanism. Ethiopia has been undertaking the second cycle peer review by two states parties of conference (COSP) and very recently finalized the processes during In-Country Visit conducted in April 14-16, 2026. The Second Cycle Review focuses on two critical pillars of anti-corruption efforts: Preventive Measures (Chapter II) and Stolen Asset Recovery (Chapter V). This review was conducted through a constructive peer-review process, where two fellow States Parties assess national systems, institutions, and practices. The process included a self-assessment, expert desk review, and direct dialogue—often complemented by a country visit.

ወደ ገጽ 2 የዞረ...

## አመራሩ ሙስናን የመታገል ተግባርን እንደ መደበኛ ሥራው ሊቆጥረው ይገባል





ሀገር በእድገትና በብልጽግና ጎዳና ላይ ባለችበት ወቅት ሙስና አብሮ የማደግ ፍላጎት ስላለው፣ አመራሩ ይህንን ስጋት የመመከት ተግባርን እንደ መደበኛ የሥራው አካል አድርጎ ሊሠራው እንደሚገባ ተገልጿል። የጠ/ሚ ጽ/ቤት የሴክተሮች እና ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ክትትል ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር ዶ/ር አክሊሉ ታደሰ ባስተላለፉት መልዕክት፣ "ሙስናን መታገል እንደ አንድ ተጨማሪ ሥራ ሳይሆን እንደ መደበኛ የሥራችን አካል አድርገን ልንሠራው ይገባል" ብለዋል። አመራሩ በንጽህና የመወሰን አቅሙን በማሳደግና ለሥነምግባር ተገዢ በመሆን ለፀረ-ሙስና ትግሉ ስኬታማነት አርዓያ ሊሆን እንደሚገባም ገልጸዋል።

ወደ ገጽ 3 የዞረ

## ኮሚሽኑ በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት በ46 የእርሻ ትራክተሮችና ተጓዳኝ ማሽነሪዎች ግዥ ጨረታ ሂደትን አቋረጠ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ በ46 የእርሻ ትራክተሮችና ተጓዳኝ ማሽነሪዎች ግዥ የጨረታ ሂደትን አቋረጠ። ኮሚሽኑ በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጥር ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ ሂደቱ እንዲቋረጥ የማድረግ ስልጣን አለው። በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት የ46 የእርሻ ትራክተሮችና ተጓዳኝ ማሽነሪዎች ግዥ ግልፅ ጨረታ ሂደትን እንዲቋረጥ አድርጓል። ለግዥ ሂደቱ መቋረጥ ምክንያት ከሆኑ የጥናት ግኝቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የእርሻ ትራክተሮችና ተጓዳኝ ማሽነሪዎችን ለመግዛት የገበያ ዋጋ ጥናት አለማድረግ፣

ወደ ገጽ 3 የዞረ

UNCAC SECOND... ከገጽ 1 የዞረ

## INTERNATIONAL COOPERATION AND PEER LEARNING

The engagement with peer reviewing countries reflected the spirit of mutual trust, equality, and shared responsibility that underpins UNCAC. The review process was undertaken based on the culture of non-adversarial and non-punitive; focused on identifying good practices, gaps, and technical assistance needs; and designed to promote experience-sharing and international cooperation. Through this collaborative exercise, valuable insights were exchanged to strengthen national anti-corruption frameworks and align them with international standards.







## FROM REVIEW TO REFORM

The UNCAC review mechanism serves as a global benchmark for assessing progress and guiding reforms. It generates a comprehensive country review report; an executive summary (will be publicly available) and actionable recommendations to enhance institutional effectiveness. These outcomes support evidence-based policymaking and reinforce accountability mechanisms across sectors.

## STRENGTHENING TRANSPARENCY AND IMPACT

The second cycle review—extended to ensure inclusivity and quality—continues to advance global anti-corruption efforts, with stronger emphasis on transparency, stakeholder engagement, and follow-up implementation.







## COMMITMENT TO ACTION

Our country reaffirms its strong commitment to implementing UNCAC provisions effectively; enhancing preventive systems and safeguarding public resources; promoting transparency, citizen engagement, and institutional integrity. We extend our sincere appreciation to the peer reviewing countries, experts, and partners for their constructive collaboration and valuable contributions throughout this process.

## MOVING FORWARD

The UNCAC Second Cycle Review is not an endpoint—but a strategic step toward sustained reform, stronger institutions, and a corruption-resilient society. Together, through partnership and accountability, we shall continue advancing the global fight against corruption.







## Recognition and Appreciation of Key Stakeholders

The Federal Ethics and Anticorruption Commission of Ethiopia, as the national representative to the Conference of the States Parties (COSP) to the United Nations Convention against Corruption (UNCAC) appreciates the stakeholder institutions and their respective focal persons for dedication and commitment during the whole review processes in delivering the required information and direct dialogues.

Ministry of Finance, Ministry of Justice Ethiopia, Federal Police Commission, Federal Procurement and Property Administration Agency, Ethiopia Civil Service Commission, Finance Intelligence Service, National Bank of Ethiopia, Delegates from Civil Society Organizations And Representative from media;

## አመራሩ ሙስናን የመታገል ተግባርን... ከገጽ1 የዞረ





የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ክቡር ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው፣ የኮሚሽኑ ዋነኛ ትኩረት የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ፣ ሙስናን አስቀድሞ መከላከል እና በሙስና ወንጀል ከሌሎች የፍትህ ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ በትብብር መስራት መሆኑን ጠቅሰዋል:: ኮሚሽኑ ከፌዴራል ፖሊስና ከዓቃቤ ሕግ ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን የገለጹት ም/ኮሚሽነሩ፣ የአመራሩ ቁርጠኝነት የታከለበት የሕግ ማስከበር ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል::ይህ የተባለው የአስተዳደር ዘርፍ ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር ባዘጋጁት የአመራሮች ስልጠና ላይ ነው:: “የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት ለፀረ-ሙስና ትግል ያለው ፋይዳ” በሚል መሪ ቃል በፕሬዝዳንት ጽሕፈት ቤት በተካሄደው በዚህ መድረክ ላይ፣ የሕዝባዊ ተቋማት ዋነኛ ግብ ሕዝብን በቅንነት ማገልገል ሊሆን እንደሚገባ ሰፊ ውይይት ተደርጓል::

በመድረኩ ላይ የቀረበው የውይይት መነሻ እንደሚያሳየው፣ አመራሩ ከመደበኛ ውሳኔ አሰጣጥ ባለፈ ለሥነምግባራዊ ውሳኔዎች ትኩረት መስጠት ይኖርበታል:: መደበኛ ውሳኔዎች በብቃትና በውጤት ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ሲሆን፣ ሥነምግባራዊ ውሳኔዎች ግን ፍትሐዊነትን፣ ትክክለኛ መረጃን እና የብዙኃኑን ተጠቃሚነት ማዕከል ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው ተመላክቷል:: ይህም በተቋማት ውስጥ ፍትህን ለማረጋገጥና የሕዝብን አመኔታ ለማግኘት ቁልፍ መሆኑ ተገልጿል::በግዥ ሂደትና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት የዲጂታል አሠራሮችን ማስፋፋት አስፈላጊ መሆኑ በመድረኩ ተነስቷል:: በተለይም በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ (e-GP) ላይ የሚታዩ ስህተቶችን ለመቀነስ ከመወሰን በፊት ጥንቃቄ የተሞላበት የገበያ ጥናት ማካሄድ እና መረጃዎችን በአግባቡ መሰብሰብ እንደሚገባ ተጠቁሟል:: “ከሰው ይልቅ ሲስተምን ማመን ይሻላል” የሚለው ሃሳብ በሰፊው የተንጸባረቀ ሲሆን፣ ቴክኖሎጂውን የሚመራው አመራር ግን ለሕግና ለሥርዓት ያለው ቁርጠኝነት ሊታከልበት እንደሚገባ አጽንኦት ተሰጥቶበታል:: በመድረኩ ማጠቃለያ ላይ እንደተገለጸው፣ ማንኛውንም የጥቅም ግጭት በግልጽነት መፍታት፣ የአሠራር ሥርዓቶችን በየጊዜው መፈተሽ እና ሥልጣንን አላግባብ የመጠቀም ዝንባሌን መግራት ከአመራሩ የሚጠበቅ ተግባር ነው:: በሥልጠናዊ ውይይቱ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች ተሳትፈውበታል::

## ኮሚሽኑ በአስቸኳይ የሙስና... ከገጽ 1 የዞረ

የግዥ ጨረታው ከመውጣቱ በፊት የኢንስቲትዩቱ ምስጢራዊ መረጃ መውጣቱና የተቋሙ ባለሙያ ምስጢር የመጠበቅ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ፣ የጨረታ ሂደቱ የጥቅም ግጭት የታየበት መሆኑ፣ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንደሚቋቋም የተደነገገ ቢሆንም አለመተግበሩ፣ ኢንስቲትዩቱ የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት ውጤት ምላሽ ሳይጠብቅ ጨረታውን በመሰረዝ ለቀጥታ ግዥ ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ግብርና ሚኒስቴርን የጠየቀ መሆኑ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው::



እንዲሁም ግብርና ሚኒስቴር ለተቋሙ ልዩ የቀጥታ ግዥ ፈቃድ ሲሰጥ የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን አዋጅ 1333/2016 አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 1 ፊደል ተራ “ሐ” መስሪያ ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ችግር ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የሚፈለገው አቅርቦት በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ማሳካት ያልተቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ የሚለውን ድንጋጌ የጣሰ መሆኑ፣ ኢንስቲትዩቱ ጨረታውን ባካሄደበት ወቅት ተወዳዳሪ ከነበሩት ተጫራች ድርጅቶች መካከል አንዱ ከሆነው እና የቴክኒካል መመዘኛ መስፈርቱን ሳያሟላ በመቅረቱ ከዉድድር እንዲወጣ ከተደረገዉ የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ልዩ የቀጥታ ግዥ እንዲፈፀም በቀን 18/05/2018 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 01/አጠ20/1/64 ግብርና ሚኒስቴር የፈቀደ መሆኑ የሚሉት በጥናት ግኝቱ የተመላከቱ ናቸው::

በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ አመራሮች እና የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት የግዥ ጨረታ ሂደቱ የጥናት ግኝት ሪፖርት ቀርቦ ግምገማ የተደረገ ሲሆን፣ በግኝቶቹም መግባባት ላይ ተደርሷል:: በቀጣይ በተቋሙ የሚከናወኑ የግዥ ሂደቶች ከሙስና እና ብልሹ አሠራር የጸዱ ሆነው እንዲፈጸሙ የሚያስችል ምክረ-ሐሳብ ተሰጥቷል::

## በአገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት የአገልግሎት አሰራር ሥርዓት ግልጽነት ላይ በተደረገ ጥናት ውይይት ተካሄደ





የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት የአገልግሎት አሰራር ሥርዓት ግልጽነት ላይ ያጠናውን ጥናት ለትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች አቅርቦ ውይይት ተካሂዶበታል:: ጥናቱ በአገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ አሰራሮችን በመለየትና የመፍትሔ ሀሳቦችን በማቅረብ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን ላይ ትኩረት ያደረገ ነው::

በውይይት መድረኩ የተገኙት የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አለሙ ስሜ (ዶ/ር) ሀገራችንን ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ ለማድረግ በቅንጅት በመስራት የተጀመረውን ለውጥ እውን ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል:: ኮሚሽኑ በየጊዜው በመልካም አስተዳደር እና በብልሹ አሰራር ላይ ጥናቶችን በማጥናት ምክረ ሀሳቦችን በመስጠት ሙስናን አስቀድመን እንድንከላከል እያገዘን በመሆኑ ሊመሰገን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል:: ሰዎች ላይ የሚፈጠሩ አደጋዎች የሚደርሰው የአሽከርካሪዎች የሥነምግባር ችግርና የመኪኖች የቴክኒክ ምርመራ በየጊዜው አለማድረግ ነው:: ይህን ችግር ለመቅረፍም ከሠው ንክኪ ውጭ የሆነ ዲጂታል አሰራር እየዘመነ መሆኑን ጠቁመዋል:: በዘርፉ ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከልም አሰራሮችን የማዘመን፣ ህጎችን የማሻሻል እና የአገልግሎት አሰጣጥን ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራ ላይ ትኩረት አድርገን እየሰራን ነው ብለዋል::

በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው በበኩላቸው በዓለምአቀፍ ደረጃ አገራት በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና በማህበራዊ ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርገው በመስራታቸው



ሙስናን መከላከል ላይ ለውጥ እንዳመጡ ተናግረዋል:: ኮሚሽኑም በበጀት ዓመቱ በተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጥናቶችን በማካሄድ ምክረ ሀሳብ እየሰጠን ነው:: በዚህም ተቋማት የሪፎርማቸው አካል በማድረግ ለውጥ እያመጡ ነው ብለዋል:: ይህ ጥናትም በአዲስ አበባ ከተማ 5 መናሃሪያዎች፣ በሀዋሳ እና በጅማ ከተማ የህዝብ ማመላለሻ መነሃሪያዎች ላይ ትኩረት ማድረጉን ጠቁመው፤ በጥናቱም ክፍተቶችን በመለየት በቀጣይ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን በመገንዘብ ቀዳዳዎችን ለመድፈን ያግዛል ብለዋል::

ም/ኮሚሽነሩ አክለውም፣ በተቋማት ላይ በየጊዜው በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጥናቶችን የምናካሄደው የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን አስቀድሞ ለመከላከል መሆኑን ጠቁመዋል::የዘርፉን ሥራ ውጤታማ ለማድረግ የሠው ኃይል ግንባታ ብሎም ሥነምግባራዊ አመራር ማፍራት ይገባል:: ጥናቱ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ አለመደረግ፣ የአሽከርካሪዎች የሥነምግባር ችግር መኖር እና የመንጃ ፍቃድ አሰጣጥ ወጥነት አለመሆኑን ስለሚያመለክት ችግሩን ለመቅረፍ ከወዲሁ መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል::

የሚንስቴሩ ሚንስትር ዴኤታ በረኦ ሀሰን አጥኚው ቡድን ሥነምግባራዊ በሆነ መልኩ ጥናቱን ማካሄዱ ሊመሰገን ይገባል፤ ጥናቱንም እያካሄድን ላለው የሪፎርም ሥራ በግብዓትነት እንጠቀማዋለን ብለዋል:: ከዚህ ባለፈም በስድስቱ ተርሚናሎች የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ነቅሰን በማውጣት ቀዳዳዎችን ለመድፈን እየሰራን ነው፤ በተለይ አንዳንድ ተርሚናሎች ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ በመሆናቸው ቀዳዳዎችን ለመድፈን ትኩረት በማድረግ እየተሰራ መሆኑን አመላክተዋል::

የጥናት ሪፖርቱ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያጋልጣሉ ያላቸውን 27 የሚሆኑ ግኝቶች ያመላከተ ሲሆን፣ ለእነዚህም የመፍትሔ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል:: በውይይቱ ሙስናን ለመከላከል ከሚረዱ መንገዶች አንዱ በጥናት የተደገፉ ስራዎችን መስራት እንደሚያስፈልግ የተጠቆመ ሲሆን፣ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ ማስደገፍ እንደሚገባም ተመላክቷል:: ተሳታፊዎች የተለያዩ ሀሳቦችን አንስተው በተሰጣቸው ምላሽና ማብራሪያ መግባባት ላይ ተደርሷል::



በጥናቱ ከታዩና ከተለዩት ክፍተቶች መካከል ለአብነት የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥና የቴክኒክ ምርመራ አውቶሞቲቭ በሰለጠኑ ባለሙያዎች አለመመርመር፣ ዕቃዎች የታሪፍ ስታንዳርድ የተሽከርካሪው ባለቤት በፈለገው ዋጋ ማስከፈሉ፣ የጫኝና አውራጅ አሠራር ለጥቅም ግጭት የተጋለጠ መሆኑ፣ በህገ ወጥ መንገድ ከተፈቀደው ታሪፍ በላይ ተጨማሪ ማስከፈሉና ብልሹ የሆነ የስምሪት አሠራር መኖሩ የሚሉት ተመላክተዋል:: እንዲሁም የአሰራር ሥርዓቱ በተሟላ ዘመናዊ ቴክኖሎጅ ያልተደገፈና ዘርፉን የሚመጥን የሰለጠነ የሰው ኃይል የሌለው መሆኑ፣ አሽከርካሪዎች እና ረዳቶች ላይ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ፣ የልዩ ባስ አገልግሎት ምቹ የመጫኛ ቦታ አለመሆን፣ የተገልጋይ እንግልት፣ ተገልጋዮች ለወከባና ዝርፊያ የተዳረጉ መሆናቸው በጥናቱ ከተስተዋሉ ግኝቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው:: በውይይቱ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አለሙ ስሜ(ዶ/ር)፣ ሚንስትር ዴኤታዎችና የዘርፉ ከፍተኛ አመራሮች ተገኝተዋል::

# በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የከፍተኛ አመራሮች ስልጠና ተካሄደ





‹‹የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግል ያለው ፋይዳ!›› በሚል መሪ ቃል የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለዘርፉ የከፍተኛ አመራሮች ስልጠና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አዳራሽ ተካሂዷል:: በተቋማት ውስጥ የፀረ-ሙስና ትግሉን የከፍተኛ አመራሩ በበላይነት ሊመራው እንደሚገባ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ በመክፈቻ ንግግራቸው አስገንዝበዋል::

ስልጠናው አመራሮች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ የጥቅም ግጭትን በመከላከልና ሥነምግባራዊ ውሳኔ እንዲሰጡ የሚያስችል አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፣ ‹‹ይህ ስልጠና የጥቅም ግጭትን ለማስተዳደር የከፍተኛ አመራሩን ሚና ያሳያል›› ብለዋል:: በስልጠናው ወቅት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ዴኤታ ክብርት ፎዚያ አሚን እንዳሉት፣ ከዚህ ቀደም በሥነምግባር ግንባታ፣ ሙስና መከላከል እና የሙስና ወንጀሎች ላይ የተሰጡ ስልጠናዎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለውጥ እያመጡ ስለሆነ ለወደፊትም ስልጠናውን አጠናክረው መቀጠል እንደሚገባ ገልጸዋል::

ተሳታፊዎች በውይይት ወቅት ሙስና በአሁኑ ወቅት ምን ላይ ነው የሚል ጥናት ያስፈልጋል፣ የኮሚሽኑ አወቃቀር ግቡን ለማሳካት በቂ እንደሆነ እና ስልጣኑን ለማጠናከር ምን እንደሚያስፈልግ ጥያቄ አንስተዋል:: በተጨማሪም በጨረታዎች ላይ ሙስናን ለማስወገድ ቴክኖሎጂን እና አሰራርን ማዘመን፣ የሀብት ምዝገባን ማጠናከር፣ አመራሩ አርዓያ መሆን እና በዲጂታል ሥርዓቶች ሙሉ በሙሉ መስራት እንደሚገባ አስተያየት ሰጥተዋል:: ‹‹የተበላሸ አመራር የተበላሸ ውጤት ያመጣል፤ አመራሩ ከተበላሸ ሰራተኛውም ያው ነው የሚሆነው›› ያሉት ክብርት ሚኒስትር ድኤታ በተለይ እንደ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ አርዓያ መሆን




እና ሆን ተብሎ የሚፈጸሙ ተግባራትን ተገቢ ቅጣት ያገኛሉ ብለዋል::

ይህ ስልጠና የከፍተኛ አመራሮችን ሥነምግባራዊ አቅም ለማጠናከርና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናን ለመከላከል የሚያደርገውን ጥረት የበለጠ ያጠናክራል ተብሎ ይጠበቃል:: ክብርት ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ ፎዚያ አሚን በተጨማሪም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በዲጂታል ሽግግር የመሪነት ሚና በመጫወት ለሌሎች ዘርፎች ተምሳሌት ሊሆን እንደሚገባ አሳስበዋል:: በተለይ በኤሌክትሮኒክ ግዢ ሥርዓት (e-procurement) እና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ሙስናን በመከላከል ረገድ የሚጠበቅበትን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚችል ገልጸዋል::

ስልጠናውን የሰጡት ዶ/ር ተስፋዬ ሂርጳሳ ተቋማትን ወደ ኋላ ከሚጎትቱ ዋና ዋና ችግሮች መካከል ሙስናና ብልሹ አሰራር መሆኑን ጠቁመው፣ "ለሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት የሚሆነውን የጥቅም ግጭትን በመረዳት፣ በእውቀት ላይ ተመስርቶ እርምጃ በመውሰድ መታገል ይገባል" ብለዋል:: በዚህ ስልጠና የተገኙት ከፍተኛ አመራሮች ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናን ለመከላከል ያላቸውን ቁርጠኝነት በመግለጽ፣ በቅርቡ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ የተሟላ ዲጂታል ግልጽነት ስርዓት ለመዘርጋት እንደሚሰሩ ቃል በቃል አረጋግጠዋል::



# ኮሚሽኑ በፌደራል ተቋማት የንብረት አያያዝና አወጋገድ አሰራር ሥርዓት ግልጽነት ላይ ያካሄደውን ጥናት ለገንዘብ ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች አቀረበ

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በፌደራል ተቋማት የንብረት አያያዝና አወጋገድ አሰራር ሥርዓት ግልጽነት ላይ ያጠናውን ጥናት ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች አቅርቦ ውይይት አካሄደ::

በውይይት መድረኩ የተገኙት በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው ኮሚሽኑ በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ፣ በሙስና ቅድመ መከላከልና ህግ ማስከበር ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን በመግለጽ ከዚህ አንፃር በበጀት ዓመቱ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ዘርፍ ተኮር ጥናት በማካሄድ ለተቋማቱ ምክረ ሀሳብ እያቀረብን የሪፎርማቸው አካል በማድረግ ለውጥ እያመጡበት ነው ብለዋል::

ም/ኮሚሽነሩ አክለውም በሙስና የሚሳተፉ ግለሰቦችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ከፌደራል ፖሊስና ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት እየተሰራ እንደሆነም ጠቁመዋል:: ጥናቱ ተቋማት በቂ ንብረት እያላቸው ሌላ ግዥ መፈጸም፣ በየጊዜው የንብረት ቆጠራ አለማድረግ፣ ህጋዊ አሰራሮችን ሳይከተሉ ንብረት ማስወገድ እና በግዥ የሚቀርቡ እቃዎች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ የሚሉ ክፍተቶችን ስለሚያመላክት ችግሩን ለመፍታት በቀጣይ ትኩረት በማድረግ መስራት ይገባል ብለዋል::

የተቋማት አመራሮችም ሙስናን ለመታገል በቅንጅት ከመስራት ባለፈ በባለቤትነት መምራት እንደሚገባቸው አሳስበዋል:: የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ ፍቃዱ ሆረታ በበኩላቸው የጥናቱ ግኝቶች በቀጣይ ለምንሰራቸው አጋዥ ይሆናሉ፤ ችግሩን ለመቅረፍም በርካታ ተግባራት እየተሰሩ ቢሆንም ሙስናን ጨርሶ ማስወገድ አልቻልንም ብለዋል:: ሙስናን ለመከላከል አመለካከት ላይ መስራት ይኖርብናል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ችግር ፈጥረው የተገኙትን ተጠያቂ



ለማድረግ ተቋማችንን በጥልቀት በማየት ሌቦችን ማጋለጥ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል::

ሚኒስትር ዴኤታው አክለውም መንግስት በሙስና ድርጊት የሚሳተፉ ግለሰቦችን ተጠያቂ የማድረግ ሥራን ማስቀጠል አለበት:: በዘርፍ ደረጃም አሰራሮችን በማዘመንና ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ማስወገድ አለብን ብለዋል:: የኮሚሽኑ ሙስና መከላከል ጥናት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው በበኩላቸው ጥናቱ በፌደራል ተቋማት የንብረት አያያዝና አወጋገድ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ አሰራሮችን በመለየትና የመፍትሔ ሀሳቦችን በማቅረብ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል::

የጥናቱ ሪፖርት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያጋልጣሉ ያላቸውን 11 የሚሆኑ ግኝቶች ያመላከተ መሆኑን ገልፀው፣ ለእነዚህም የመፍትሔ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል ብለዋል:: በጥናቱ ከታዩና ከተለዩት ክፍተቶች መካከል ለአብነት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ አለመወገድ፣ መጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ ኬሚካሎች በወቅቱ አለመወገድ፣ የሚወገዱ ንብረቶች አቀማመጥ ሌሎችበንብረቶች



ላይ ጉዳት እያደረሰ መሆኑ፣ ህጋዊ አሰራርን ሳይከተል ንብረት መወገዱ፣ የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ በአግባቡ ተደራጅቶ አለመያዝና አዲስ ከሆኑት ጋር ተቀላቅለው መያዛቸው በንረት ማስወገድ ወቅት አ አብረው የሚወገዱበት ዕድል የሚፈጥር መሆኑ፣ እንዲሁም በግዥ የሚቀርቡ ዕቃዎች ላይ ተገቢ ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ የሚሉት ተመላክተዋል::

እንዲሁም አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በወቅቱ አለማስወገድ፣ የሚወገዱ ንብረቶችን ለማስወገድ የሚወጣ የጨረታ ሂደት ተደራሽና አሳታፊ አለመሆን፣ በንብረት አወጋገድ ላይ የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር አለመጠናከር እና የንብረት አስተዳደር መመሪያ በአግባቡ አለመተግበሩ በጥናቱ ከተስተዋሉ ግኝቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው:: በውይይቱ የገንዘብ ሚኒስቴርና በስሩ ተጠሪ የሆኑት የመንግስት ግዥ አገልግሎት፣ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ፣ እዳና ሀብት ኮርፖሬሽን ከፍተኛ አመራሮች የተገኙ ሲሆን፥ የተለያዩ ሀሳቦችን አንስተው በተሰጣቸው ምላሽና ማብራሪያ መግባባት ላይ ተደርሷል::

# ሥነ-ምግባራዊ የቢዝነስ ውሳኔ ሰጪነት ለባንክ የፋይናንስ አፈፃፀም ቁልፍ ድርሻ አለው ተባለ





ሥነ-ምግባራዊ የቢዝነስ ውሳኔ ሰጪነት ለባንካችን የፋይናንስ አፈፃፀም ቁልፍ ድርሻ አለው ሲሉ የዓባይ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ ገለፁ፡፡ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ይህን የተናገሩት የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዓባይ ባንክ ጋር በመተባበር ”የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ!‘ በሚል መሪ ቃል ለባንኩ ከፍተኛ አመራሮች በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና በጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር ዙሪያ በተዘጋጀው ስልጠና መድረክ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ነው፡፡ ዋና ስራ አስፈፃሚው አያይዘውም በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ያተኮረ ሥልጠና መሰጠቱ ለውጤታማ የፋይናንስ አፈፃፀም ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው ገልፀዋል፡፡ በየዕለት ተዕለት ስራዎቻችን የምንወስናቸውን ውሳኔዎች እንደ አገላጋይና ተገልጋይ ሆነን ማየት ይኖርብናል ብለዋል፡፡ አንድ አመራር በመጀመሪያ እንደ አገልጋይ እራሱን በሥነ-ምግባር መነፀር ማየት እና ለተገልጋዮች ታማኝ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የሥልጠናውን አስፈላጊነት በገለፁበት ንግግራቸው ሥነ-ምግባርን ማስተማር ሰወች ሳያውቁ ሙስና እንዳይፈፅሙ ትልቅ ግንዛቤ የሚፈጥር በመሆኑ በሁሉም ተቋማት ሊቀጥል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ ውጭ ላይ ያለው የሥነ-ምግባር መጓደል ውስጥ በተቋማት የውስጥ አሰራር ላይ ጉዳት እንዳያመጣ ሁሉም በየደረጃው ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ እንደ ዓባይ ባንክ ሰው እንዳይሳሳት ቀድመን እናስተምራለን ነገር ግን ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥን የሚጥስ አመራርና ሰራተኛ ካለ የሚወሰደው ህጋዊ ርምጃ ከባድ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ የባንኩን መርህ ከአስራ ሁለቱ የሥነ-ምግባር መርሆዎች ጋር በማስተሳሰር እየሰሩ እነደሆነም አክለው ገልፀዋል፡፡

በፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥልጠና መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ የኋለሽት ደሳለኝ በበኩላቸው የሰው ምክንያታዊነት (Rationalization) ሲጨምር ትክክለኛና ሥነ-ምግባዊ ውሳኔዎችን የማሳለፍ አቅሙ ይጨምራል ብለዋል፡፡ ሙስናን ምክንያታዊ ማድረግ እጅግ አደገኛ ነው ያሉት መሪ ስራ አስፈፃሚው፣ ውሳኔን እንጅ ሙስናን ምክንያታዊ ማድረግ ተገቢ እንዳልሆነ አስገንዝበዋል፡፡ ለሥነ-ምግባራዊ ውሳኔዎች ከሌሎች መደበኛ ውሳኔዎች የተለየ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል ሲባልም ሁኔታዎችን በምክንያታዊነት በመተንተን ለምንወስናቸው ውሳኔዎች ማስረዳት እንድንችል ስለሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሥነ-ምግባር ሥልጠናው የሚያስፈልገውም በምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የማስተላለፍ ብቃት እንድናዳብር ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ሙስና የገንዘብና የሥልጣን አቅም ባላቸው አካላት ጭምር የሚፈፀም በመሆኑ ትግሉ ከባድ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፣ አመራሮች ከሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋር በተባበር በሶስቱም የጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ አያይዘውም መንግስት በ2030 ሁሉንም አገልግሎቶች ዲጅታላይዝድ ለማድረግ ባስቀመጠው ስትራቴጅክ እቅድ መሰረት ተቋማት አሰራራቸውን ሙስናን መከላከል በሚያስችል መልኩ ማዘመን ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡ የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም በዚሁ ልክ አሰራሩን ለማዘመን ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በሥልጠናው ውይይት ወቅት ከሥላጠናው ተሳታፊዎች በርካታ ሃሳቦችና አስተያየቶች የተነሱ ሲሆን፣ በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል ዙሪያ ሥልጠናው መሰጠቱ በጉዳዩ ላይ ወሳኝ ግንዛቤ እንደፈጠረላቸው ገልፀዋል፡፡ ማንኛውም ሥራ ከግንዛቤ ፈጠራ ነው የሚጀምረው፣ ነገር ግን ሙስናን በግንዛቤ ፈጠራ ብቻ መቀነስ ስላማይቻል ከሰው ንክኪ ነጻ የሆነ አሰራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ሙስናን ከሚያባብሱ ሁኔታዎች መካከል የግለሰቦች መጥፎ ባህሪይና ፍላጎት ብቻ ሳይሆን የተቋማት አሰራር ለሙስና ተጋላጭ መሆኑ ነው ሲሉም ተሳታፊዎቹ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ከግንዛቤ ፈጠራ እና ሲስተምን ተግባራዊ ከማድረግ ባሻገር በተጠያቂነት እና ህግ ማስከበር ላይ በርካታ ስራ መሰራት እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡ ጥሩ ይሰራል እና ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ ያሳልፋል ብልን ሀላፊነት ቦታ ላይ ያስቀመጥነው ሰው ከማይጠበቅ ቦታ ላይ ሲገኝ ተጠያቂ ማድረግ ሲቻል ጭምር ነው የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ የሚያደርገው ብለዋል፡፡

በመጨረሻም አጠቃላይ በሥልጠናው መሰረታዊ ሀሳቦች ላይ ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎች በአሰልጣኝ ዶ/ር ተስፍዬ ሄርጳሳ እና በአቶ የኋላእሸት ደሳለኝ በቂ መልስና ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን፣ የባንኩ ዋና ስራ እስፈጻሚ አመራሮች ከስልጠናው ያገኙትን እውቀት ወደተግባር ለውጠው ስራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡



## ኮሚሽኑ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሥነምግበርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር በዲጂታል ሀብት ምዝገባና ጥናት ዙሪያ የቨርቹዋል ውይይት አካሄደ


የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሥነምግበርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር በዲጂታል ሀብት ምዝገባና ጥናት ሥራዎች ዙሪያ የቨርቹዋል ውይይት አካሂዷል፡፡ በውይይቱ በ2018 በጀት ዓመት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአመራርና ሰራተኛ የዲጂታል ሀብት ምዝገባ የ9 ወራት አፈጻጸም ቀርቦ የተገመገመ ሲሆን፣ በአፈጻጸማቸው በከፍተኛ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ዩኒቨርስቲዎችን ለመለየት ተችሏል፡፡

በውይይቱ በበጀት ዓመቱ የአመራርና ሰራተኛ የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ያላጠናቀቁ ዩኒቨርስቲዎችም እስከ ግንቦት 10/2018 ዓ.ም አስመዝግበው መጨረስ እንዳለባቸው መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በተጨማሪም፣ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ‹‹በዩኒቨርስቲዎች የውስጥ ገቢ አስተዳደር የአሰራር ስርዓት ግልጽነት›› በሚል ርዕስ በሚጠና ጥናት ላይ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያስችል ዘንድ ውይይት ተደርጓል፡፡




ጥናቱ የመካከለኛው ዘመን (2016-2018 ዓ.ም) የውስጥ ገቢ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ የተገኘ ገቢ ምን ያህል እንደሆነና የገቢው አይነት ምን እንደሆነ በመለየት ዩኒቨርስቲዎች የአሰራር ስርዓቶችን እንዲያስተካክሉ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በውይይቱም በዲጂታል ሀብት ምዝገባ ያጋጠሙ ችግሮችና የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች የተቀመጡ ሲሆን፣ ከተሳታፊዎች ሀሳብና አስተያየቶች ተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡





# ሙስናን መከላከል የሀገርን ገፅታ መገንባትና የቱሪዝም ገቢን ማሳደግ ነው - ክቡር እንደገና አበበ(ፒ.ኤች.ዲ)





የቱሪዝም ሚኒስቴር ከፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር ለከፍተኛ አመራሮች ‹‹የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ!›› በሚል መሪ ቃል በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና በጥቅም ግጭት አያያዝ ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጥቷል፡፡ በመድረኩ ላይ የተገኙት የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር እንደገና አበበ(ፒ.ኤች.ዲ) እንደገለጹት፣ ሙስናን መከላከል ለቱሪዝም ዘርፉ እድገትና ለሀገር ገፅታ ግንባታ ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰው፣ አመራሩ ከውጭ ከመጠበቅ ይልቅ ወደ ውስጥ በመመልከት ራሱን መፈተሽና ከስልጠናው ያገኘውን እውቀት በተግባር ማዋል እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው፣ አመራሩ በዕለት ተዕለት ተግባሩ ለጥቅም ግጭት ተጋላጭ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመው፣ ይህንን እንዴት ማስተዳደር እንዳለበት ግንዛቤ መያዙ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አክለውም አመራሩ በሥነ-ምግባር ግንባር ቀደም ሆኖ በመገኘት ለሠራተኞቹ አርዓያ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸው፣ ስልጠናው እስከ ታችኛው የሠራተኛ እርከን እንደሚወርድ አረጋግጠዋል፡፡

ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የመጡት አሰልጣኝ ዶ/ር ዮሀንስ ጴጥሮስ ባቀረቡት ገለፃ፡ ሙስና ድንበር ተሻጋሪና ከጥቅም ግጭት የሚመነጭ መሆኑን፤ የጥቅም ግጭት የመንግስት ስልጣን ባለበት በማንኛውም ቦታ ሊከሰት እንደሚችል፤ ሀብት ማፍራት ሕገ-መንግስታዊ መብት ቢሆንም፣ ጥያቄ የሚነሳው ግን በአፈራር ሂደቱ ላይ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

የስልጠናው ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት፣ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ መረጃን መሰብሰብና ስጋቶችን መቀነስ እንደሚገባ፤ ከሕግና ደንብ ባሻገር ሞራላዊ እሴቶችን ማገናዘብ አስፈላጊ መሆኑን፤ በተለይ በቱሪዝም ዘርፍ ፈጣን ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ከጥቅም ግጭት ጋር ሳይጋጩ እንዴት መፈጸም እንዳለባቸው ጥያቄዎችን አንስተዋል፡፡ ከውጭ የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን በማስቆም ረገድ የተወሰዱ እርምጃዎች ለአርዓያነት የሚጠቀሱ መሆናቸው ተመላክቷል፡፡

በመጨረሻም ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ስለሽ ግርማ ባስተላለፉት መልዕክት፣ በቀጣይ በሚደረጉ ማሻሻያዎች በግዥ፣ በሆቴል ደረጃ ምደባ እና በሕገ-ወጥ አደን ዙሪያ ያሉ የጥቅም ግጭቶችን በጥብቅ መከታተል ይገባል ብለዋል፡፡ የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል የ"መሶብ" የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በቴክኖሎጂ ማዘመን፣ በዚህ በጀት አመት ስልጠናውን እስከ ታችኛው መዋቅር በማውረድ የግል ዘርፉንም ማሳተፍ፣ ከሥነምግባር አለፍ ሲል የሕግ ተጠያቂነትን ማረጋገጥና በህጻናትና ወጣቶች የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ላይ በትኩረት መስራት እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡



## በክልሉ በሙስና ወንጀል የተከሰሱ ግለሰቦች በእስራትና በገንዘብ ተቀጡ



በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን ኪንዶ ኮይሻ ወረዳ በሕዝብ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ላይ በተፈጸመ የሙስና ወንጀል ተከሰው የነበሩ አድማሱ ላባ፣ አሸናፊ አብርሃም እና መስፍን ማዛ የተባሉ ግለሰቦች በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተላልፎባቸዋል፡፡

ተከሳሾቹ በወረዳው የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም 1ኛ ተከሳሽ የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ክትትልና ግምገማ ኦፊሰር፣ 2ኛ ተከሳሽ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ቡድን መሪ እና 3ኛ ተከሳሽ የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም የማህበረሰብ ሥራዎች አስተባባሪና የሴፍቲኔት ግዥ ኮሚቴ አባል ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በ2017 ዓ.ም ለተጠቃሚዎች ሊከፈል የሚገባውን ገንዘብ ያለ አግባብ በሐሰተኛ ሰነድ በማጭበርበር ለማይገባቸው ግለሰቦች ክፍያ በመፈጸም ከ8.8 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግሥትና የሕዝብ ሃብት እንዲመዘበር በማድረጋቸው በዐቃቤ ሕግ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸው የክስ ሂደታቸው በፍርድ ቤት እየታዩ ቆይቷል፡፡

የክስ ሂደቱን ሲመለከት የነበረው የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረቡ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በጥልቀት ከመረመረ በኋላ ተከሳሾቹ የፈጸሙት ድርጊት የመንግሥትን አሠራር የጣሰና የሕዝብን ጥቅም የጎዳ መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

በዚህም መሠረት እያንዳንዳቸው ግለሰቦች በ7 ዓመት ከ2 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 8,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹ በሐሰተኛ ሰነድ ያባከኑት የሕዝብ ገንዘብ በፍትሐ ብሔር ክስ እንዲመለስ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔ በመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ላይ ተቀምጠው የሕዝብንና የመንግሥትን ንብረት ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉ ግለሰቦች ከሕግ ተጠያቂነት እንደማያመልጡ ማሳያ መሆኑ ተገልጿል፡፡

## ኮሚሽኑ ከኢትዮጵያ ፖስታ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ስልጠናዊ ውይይት አካሄደ

የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ፖስታ ከፍተኛ አመራሮች ጋር "የአመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ!" በሚል መሪ ቃል ስልጠናዊ ውይይት አካሂዷል፡፡ ስልጠናዊ ውይይቱ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ግልፅነትን ለማስፈንና ብልሹ አሰራሮችን ለመታገል የተጀመረውን ሀገራዊ ንቅናቄ ተከትሎ ተቋማዊ ሪፎርምን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ያለመ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በስልጠናዊ ውይይቱ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ፖስታ የዋና ሥራ አስፈፃሚ ተወካይ አቶ ጋሻው መርሻ ስልጠናው በአሁኑ ወቅት መንግስት ሙስናን የመታገል ስትራቴጂ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ባለበት ሁኔታ፣ የኢትዮጵያ ፖስታ



እንደተቋም አመራሮቹን ከአድሎአዊነትና ከጥቅም ግጭት የፀዱ ማድረግን ዓላማ ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ስልጠናዊ ውይይቱ ትኩረቱን ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭትን ማስተዳደር እና አመራሩ በማንኛውም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎች ወቅት የሕዝብንና የመንግስትን ጥቅም የሚያስቀድም እንዲሁም ሙስና የሚፈጠርባቸውን የጥቅም ግጭት ሁኔታዎች አስቀድሞ በመለየትና በመከላከል፣ ተቋማዊ ተዓማኒነትን መገንባት ላይ በማተኮር መሰጠቱ ተመላክቷል፡፡ በመጨረሻም የስልጠናዊ ውይይቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች፣ አስተያቶች እና ሀሳቦች አንስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993
ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**


---


## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

**NCRS**


## ርዕሰ -አንቀፅ

# ሥነ-ምግባራዊ አመራርነት ሙስናን ለመከላከልና ለተቋማዊ ስኬት ያለው ፋይዳ ወሳኝ ነው!

ሙስና ሥልጣንና ኃላፊነትን ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም በማዋል ሕጋዊና ሥነ-ምግባራዊ መርሆዎችን በመጣስ የሚፈጸም ማኅበራዊ ደዌ ነው፡፡ ሙስና በአንድ ሀገር ውስጥ የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎችን ከመግታት ባለፈ፣ በዜጎች መካከል ሊኖር የሚገባውን እኩልነት፣ ፍትሃዊና ሚዛናዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል ሥርዓትን ያዛባል፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ሕዝብ በመንግሥትና በተቋማት ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሸር በማድረግ ለፖለቲካዊና ማኅበራዊ አለመረጋጋት ዋነኛ መንስኤ ይሆናል፡፡

ይህ አጥፊ ተግባር የሚበቅለው፣ የሚያድገውና የሚፋፋው ደግሞ የአመራር ሥርዓቱ ከሥነ-ምግባር እሴቶች ያፈነገጠ ሆኖ ሲገኝ፣ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራር ሲዳከም ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ ሀገር ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ መኖር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህ አሰራር በሌለበት ሁኔታ ግን ዜጎች ለሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲሁም ለመልካም አስተዳደር እጦት የተጋለጡ ይሆናሉ፡፡

ሥነ-ምግባራዊ አመራርና ውሳኔ አሰጣጥ በህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዘንድ በሥነምግባር እሴቶች የሚመራና ተቋማዊ ባህል ሆኖ ማደግ እና መጎልበት ይኖርበታል፡፡መሪዎች ሌሎች ሠራተኞችን ለተቀመጠ ግብ እና አላማ ስኬት አቅጣጫ መሰጠት እና አርዓያ ሆነው የመምራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ለዚህም በመደበኛ ሥራቸውም ሆነ በማኅበራዊ ሕይወታቸው፣ በሥነምግባራቸው ለሌሎች ምሳሌ የሚሆኑ እና የሚጠበቅባቸውን በማናቸውም ጉዳዮች ሁሉ የተሻሉ ሆነው መገኘት ይገባቸዋል፡፡

መሪዎች የሚናገሩትን ሆነው በመገኘት ሰራተኞች የራስን ፍላጎት እና መነሳሳት እንዲኖራቸው አርአያ ሆነው መገኘት አለባቸው፡፡ ለተቋም ውጤታማነት መሪዎች በመልካም ሥነምግባር፣ በሥራ ፈጠራ እና አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ ለተቋሙ ማህበረሰብ አርአያ ሆነው መገኘት ይገባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ መሪዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ሥነምግባርን ተላብሰው ፍትሃዊ ውሳኔ የሚወስኑ፤ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በቁርጠኝነት የሚታገሉ፣ ህዝብን በቅንነትና በታማኝነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ ለሀገር እድገትና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጠቀሜታው ከፍተኛ ይሆናል፡፡ መሪዎች በሚወስኗቸው ውሳኔዎች ሥነምግባራዊ መርሆዎችን የሚያከብሩና የሚያስከብሩ በመሆን የግልፅነትና ተጠያቂነትን ሥርዓት በማስፈን ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚከላከሉ እንዲሁም በሚወስኗቸው ውሳኔዎች ህዝብን ማገልገል ሥራቸዉ እንደሆነ አምነው የተቀበሉ፣ ከፍተኛ የሥነምግባር ደረጃ ተላብሰው ከአድሎ፣ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የጸዳ ፈጣን፣ ጥራት እና ብቃት ያለው የህዝብ አገልግሎቶችን መስጠት የሚችሉ፣ ሥምግባራዊ ምልዑነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል የሚል መልዕክት እናስተላልፋለን፡፡



# ቆይታ

**“የቱሪዝም ዘርፉን ከሙስና ለመጠበቅ ቴክኖሎጂንና ሥነ-ምግባርን በማቀናጀት የሀገርን ገጽታ መገንባት።”**

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ**



ኢትዮጵያ ካሏት በርካታ የቱሪዝም ፀጋዎች ባሻገር፣ ዘርፉ ለሀገር ገጽታ ግንባታና ለኢኮኖሚ እድገት ያለው ሚና የላቀ ነው። ሆኖም ይህ ዘርፍ ካለው ስፋትና ውስብስብነት አኳያ ለሙስናና ለብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ እንዳይሆን ጠንካራ ተቋማዊ አሰራርን መዘርጋት የግድ ይላል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሙስናን ለመከላከልና የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን ቴክኖሎጂን እንዴት እየተጠቀመ ይገኛል? በቅርቡ አንድ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ ያሳየችው ድንቅ የታማኝነት ተግባር ለዘርፉ ምን ትርጉም አለው? በሚሉና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ከሆኑት ከክቡር ዶ/ር እንደገና አበበ ጋር ያደረገው አጭርና ፍሬያማ ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል። መልካም ንባብ!

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ፣ ራስዎን ለአንባቢያን ያስተዋውቁልን?

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ፦** ዶክተር እንደገና አበበ እባላለሁ፤ በቱሪዝም ሚኒስቴር ፕሮሞሽንና ግብይት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ነኝ።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** እንደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በሥነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ረገድ የተሰሩ ሥራዎችን ቢገልጹልን?

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ፦** እንደ መሥሪያ ቤት ዘርፉ ከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት ያለበት እና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግ፣ መሥሪያ ቤቱ ከተቋቋመ ገና አራት ዓመቱ ቢሆንም በመጀመሪያ ሲቪል ሰርቪስ በሰጠው አሰራር መሠረት ለሥነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል የሚያስችል መዋቅር ተዘርግቶ ሰው ተመድቧል። በየጊዜው (በዓመት አራት ጊዜ) ተቋሙ በተለይ የሙስና ስጋት ያለባቸውን አካባቢዎች ጥናት ያደርጋል፤ የጥናቱ ውጤትም ይፋ ይደረጋል። ጥናቱን መሠረት በማድረግ ሠራተኛው በሥነ-ምግባር እና ሙስና መከላከል ዙሪያ በሥልጠና ግንዛቤ እንዲያገኝ ይደረጋል። ከዚያ ባለፈ ደግሞ ከፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በሰፊው ሠራተኛውና አመራሩ እንዲወያዩበት ተደርጓል። ይህም ማለት የሥነ-ምግባር ግንባታ እና የፀረ-ሙስና ሥራ የአንድ ተቋም ወይም ክፍል ብቻ ሳይሆን፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በምናደርገው ግንኙነትም እንዲህ ያሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እንሠራለን።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በመሥሪያ ቤቱ ከአሁን በፊት በአቅም ግንባታ ሥልጠና ብዙ ሥራዎች እንደተሰሩ በሰጡን መረጃ ማወቅ ይቻላል። የሥልጠና ሥራዎች በመከናወናቸው በመሥሪያ ቤቱ ምን ዓይነት ለውጦች እንደመጡ ግምገማ አድርጋችኋል?

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ፦** አዎ፣ የሥልጠናው ግብረ-መልሶች ይሰበሰባሉ፤ ተሰብስበውም ይደራጃሉ፤ በዚህ መሠረትም ትንተና ተደርጎባቸዋል። ትክክለኛው ግምገማው እንዲህ ነው ማለት ባይቻልም፣ በሥልጠናው ያየነው ውጤት አንዱ በሥነ-ምግባር ማገልገል ነው። በዚህ ላይ ለውጦች አይተናል። በተለይ ደንበኛን ከማገልገል፣ ሠራተኞች ሰዓት ከማክበር እና ሙስናን ከመከላከል አኳያ ለውጦች ተመዝግበዋል። ሌላው በሠራተኞች ሪፎርም እየሠራን ነው። ሙስናን መከላከል የሚያስችል እና የደንበኞች አገልግሎት በኤሌክትሮኒክ አስተዳደር (በኢ-ገቨርናንስ) ከመጣ በኋላ ደግሞ አገልግሎት አሰጣጡ እየተሻሻለ ነው። አገልግሎት አሰጣጣችንን በተለያዩ መንገዶች ስንመረምረው ከሥልጠና በኋላ ሠራተኛው ሥራውን እያከበረ፣ ደንበኛውንም በአክብሮት እያስተናገደ ይገኛል። በአጠቃላይ ሥልጠናው በመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ላይ በሥነ-ምግባር መታነጽ እና ሙስና መከላከል ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር በሥራው ላይ አዎንታዊ ለውጦችን እያመጣ ነው።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** ሙስናን ከመከላከያ መንገዶች አንዱ የሀብት ምዝገባ ነው። አመራሩ በሀብት ምዝገባ ቀዳሚ በመሆን ምን ተግባራትን እያከናወነ ነው?

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ፦** የሀብት ምዝገባ በሁለት መንገድ ነው የተከናወነው። አንደኛው የከፍተኛ አመራሩን ከፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የመጡ አካላት በተገኙበት አስመዝግቦ አስረክቧል። ሁለተኛው የተደረገው፣ መካከለኛ አመራሩ ቢቻል በአንድ ቀን በጥቅል (ልክ እንደ ዲጂታል መታወቂያ) በአንድ ቀን እንዲመዘገብ አድርገናል። አመራሩ ብቻ ሳይሆን ሠራተኛውም እስከ ታች ወርዶ እንዲመዘገብ ተደርጓል። እስከ አሁኑ ሰዓት ድረስ መመዝገብ ያለበት አካል 100 ፐርሰንት ሀብቱን አስመዝግቧል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናን

ወደ ገጽ8 የዞረ...

ለመከላከል በመሥሪያ ቤቱ ምን እየተሠራ ነው?

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ፦** ቴክኖሎጂ የሁሉም ነገር ደም ሥር እየሆነ ነው:: ለሙስና መከላከል ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ነገሮች አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን ሙስናን ለመከላከል በየቦታው የሴኩሪቲ ካሜራዎቻችን አሉ፤ የንብረት ክፍል፣ የሠራተኛ መውጫና መግቢያ መቆጣጠሪያ፤ ይሄን በማድረግ እየተከታተልን ነው:: ይህን ማድረግ ይጠበቅብናል::

ሁለተኛው ኢ-ገቨርናንስ ነው:: ብዙዎቹን ሥራዎቻችንን በኤሌክትሮኒክስ እያከናወንን ነው:: የመሥሪያ ቤቱ ሥራዎች በብዛት 70 ፐርሰንት ደርሰዋል:: ስለዚህ ከእጅ ንክኪ ነፃ ተደርጎ ሙስናን በመከላከል ላይ ነን:: አሁን የሚቀረን ዳሽቦርድ (Dashboard) ማበልጸግ ነው:: ለምሳሌ አንድ ሠራተኛ ስንት ሰዓት ገባ? አንድ ደንበኛን በስንት ሰዓት አስተናገደ? እንዴት ሆነ? የሚለውን የምንከታተልበት ዳሽቦርድ መሥራት ነው:: ይህን ደግሞ አሁን መንግሥት በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ‹‹ሞሰብ›› የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጋር እያያያዝን ነው:: አሁን 12 አገልግሎቶች በሞሰብ ላይ አሉን፤ ከዚህ በላይ ከፍ ማድረግ እንፈልጋለን፤ እየሠራንም ነው::

ሦስተኛው ከግዥ ጋር ተያይዞ መንግሥት በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ሁሉም ግዥዎች በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ (e-GP) እንዲፈጸም በማድረግ፣ በኢ-ፍሚስ (IFMIS) ምዝገባዎች በዚያ መልኩ እየሄዱ ነው:: ብዙ ሥራዎች በቴክኖሎጂ አገልግሎት አሰጣጥን የሚቀላጥፉና ሙስናን የሚከላከሉ ሥራዎች እየተሠራባቸው ነው፤ ግን ገና አጥጋቢ አይደለም፣ ተጨማሪ ሥራን ይፈልጋል::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በመሥሪያ ቤቱ ለሥነ-ምግባር ግንባታና ለፀረ-ሙስና ትግሉ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች ካሉ ቢነግሩን?

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ፦** መሰናክል ይሆናሉ የምላቸው አንዱ ዘርፉ በጣም ሰፊ መሆኑ ነው:: አንድ ቱሪስት ከቅበላ ጀምሮ አይቶ እስኪመለስ ድረስ መዳረሻዎች ብዛት አላቸው፤ የኢሚግሬሽን፣ የአየር መንገድ እና የመዳረሻዎች ጉዳይ አለ:: ይህ ሁሉ ውስብስብ ነው::

እዚያም እዚያም መከታተልና ድጋፍ ያስፈልጋል:: ግንዛቤ መስጫ ቦታዎች ላይ ለምሳሌ ቢደረግልን ብለን የምናስበው፤ በመዳረሻ ልማት ቦታዎች ላይ አንድ ቱሪስት ከዚህ አምስት መቶ ኪሎሜትር ቢሄድ ኬላ አለ:: በኬላዎች ወይም በሌላ ቦታ በሥነምግባር ጉድለት ምክንት ቱሪስቶችን የሚያስቆጣ ነገር ይመጣል:: አላስፈላጊ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ይደረጋል:: ይህን መሰል ውስብስብ ነገሮችን የምንፈታባቸውን ዘዴዎች ከእናንተ ኮሚሽን ጋር ብንሠራ ደስ ይለናል::

ሁለተኛው፣ ብዙውን ጊዜ አይተህ ከሆነ ቱሪስቶች ከቦታ ቦታ የሚሄዱባቸው ተሽከርካሪዎች አሏቸው:: ስለዚህ ከተሽከርካሪ ግብዓቶች ጋር ይገናኛል፤ ከነዳጅ እና ከመሳሰሉት ጋር ይያያዛል:: ‹‹ነዳጅ›› ስልህ ወቅታዊ እንዲመስልህ አይደለም፣ የቆየ ችግር ነው:: ቱሪስቶች ርቀው ነው የሚሄዱት:: እዚያ አካባቢ ለመሄድ ነዳጅ ከላይ ጭነው ነው የሚሄዱት:: እነዚያ ነገሮች ለሙስና አጋላጭ ናቸው:: ስለዚህ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ላይ ከአካባቢው መስተዳድር ጋር ሥራዎችን ብንሠራ፣ ተቋማዊ መሠረተ ልማቶች ቢኖሩ ያንን ጭነው አይሄዱም:: ይሄ ለሙስና ያጋልጣልና በጋራ ብንፈታው ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ:: እነዚህን እንደ መሰናክል መውሰድ እንችላለን:: ከሁሉም በላይ ግን ባህሪ/ሥነ-ምግባር ወሳኝ ነው:: የቱሪስት መኪኖች አሽከርካሪዎች ባህሪ፣ የአስጎብኚዎች መልካም ሥነ-ምግባር መኖር ከሙስናው በላይ ሥራው የሚፈልገው ነው:: ቱሪስትን በሚገባው ቋንቋ አስተናግዶ፣ አንዴ ብቻ ሳይሆን ተመላልሶ እንዲመጣ፣ ከሄደ በኋላ ስለ ሀገራችን ጥሩ ገጽታ እንዲገነባ ስለምንፈልግ በእነዚህ ረገድ ክፍተቶች ይኖራሉ:: እነዚህን ክፍተቶች በጋራ ብንሠራ ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** የአንድ የተቋማችሁ ሠራተኛ ወ/ሮ ኤልሳቤት ተሾመ የተባለች፣ ለአንድ ቻይናዊ ጎብኝ ያገኘችውን ንብረት በመመለስ ታማኝነት አሳይታለች:: ይህ ደግሞ ከተቋም ሥነ-ምግባር ወይም ከግል ባህሪ ሊመነጭ ይችላል:: ሠራተኛዋ ታማኝነቱን ያሳየችው ከተቋም ሥነ-ምግባር የመነጨ ይሆን ክቡር ሚኒስትር?

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ፦** ይህን መለየት ይከብደናል፤ ነገር ግን ብዙ የምንሠራባቸው ቦታዎች የሀገር መልክና ገጽታዎች ናቸው:: ‹‹ይህ መሥሪያ ቤት ሳህኔ ነው፣ የምበላበት ነው፤ ስለዚህ ዛሬ ብቻ በልቼ መኖር አልፈልግም›› የሚል አመለካከት ያላቸው ሠራተኞች ነው ያሉን:: ስለዚህ ወ/ሮ ኤልሳቤት ያደረገችው ለሌሎች ሠራተኞች ምሳሌ ነው የሚሆነው:: በእርግጥ ከዛ በላይ ግን እሷ ትሠራበት የነበረው ቦታ ‹‹ሉሲ›› የምትገኝበት ቅርስ ነው:: እጅግ ውድ የሆኑና በሀገር መሪዎችና በተለያዩ ቱሪስቶች የሚጎበኙ ቅርሶች ያሉበት፣ ኢትዮጵያ ገና አጥንተን ያልጨረስናት በአርኪኦሎጂው ‹‹ምድረ ቀደምት›› ነን ብለን የምናሳውቅበት ቦታ ነው:: ይህን ደግሞ በጥናትና በምርምር ነው የምናስደግፈው::

ስለዚህ ብዙ ቱሪስቶች የሚመጡበት ቦታ ነው:: ቦታው ከሙዚየምነትም ከፍ ያለ ነው:: እዚያ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች የሚኖሩበት አንዱ ምክንያት ይሄ ነው:: ሁለተኛው፣ የእኛ ሥራ ወይም ኑሯችን የተመሠረተው ቱሪስት በመጣ ቁጥር ነው:: ቱሪስት መጥቶ አይቶ ረክቶ መሄድ ብቻ ሳይሆን፣ እንዲህ ዓይነት ሥነ-ምግባርን የተላበሱ ሰዎች ያሉበት ቦታ ሲሆን የዚያ ቦታ ዋጋ ከፍ እያለ ይሄዳል:: ይህን በማሰብ ነው:: ወ/ሮ ኤልሳቤት ጎልታ ትውጣ እንጂ እንደ እሷ ዓይነት ሰዎች በየቦታው አሉ:: ከሥራችን ጋር ተያይዞ የእሷ ጎልቶ ወጣ እንጂ አየር ማረፊያዎች አካባቢም አሉ:: ከኢሚግሬሽን ጋር ተያይዞ ቀጥታ ከቱሪስቶች ጋር የሚገናኙና በየጊዜው በሥነ-ምግባር አርዓያ የሆኑ ሠራተኞች አሉ:: ሥራውም ይህን ይፈልጋል:: ይህ ደግሞ በደንብ እየሰፋ እንዲሄድ ስለምንፈልግ እሷንም ተቋሙ እውቅና ሰጥቷታል::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ?

**ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር እንደገና አበበ፦** ይህች ሀገር በጣም ትልቅ ሀገር ነች:: የሥነ-ምግባር ሀገር ነች:: መሪዎቻችንና አባቶቻችን በሥነ-ምግባራቸው፣ በጀግንነታቸውና በሀገር ወዳድነታቸው ነው ለዚህ ያበቁን:: የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የያዘው መፈክር ‹‹ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ›› የሚል ነው:: ስለዚህ በጋራ ሠርተን ለልጆቻችን ንጹሕ፣ ሙስና የሌለባትና ሥነ-ምግባር ያለው ዜጋ የሚኖርባት ሀገር እንድናወርሳቸው መልዕክቴን ማስተላለፍ እፈልጋለሁ::

እናመሰግናለን!

# ሳይቃጠል በቅጠል

## "ሥነ-ምግባር ለሙስና መከላከል የግንብ አጥር ነው!"

የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዋና ተልዕኮ በሥነ-ምግባር የታነጸ ማህበረሰብ በመገንባት፣ ሙስና እና ብልሹ አሠራር በሀገሪቱ ልማትና መልካም አስተዳደር ላይ የሚያደርሱትን እንቅፋት መከላከል ነው:: ይህንን ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ ደግሞ ሥነ-ምግባርን እንደ ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ መሣሪያ ይጠቀማል::

"ሥነ-ምግባር ለሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከል የግንብ አጥር ነው" የሚለው አባባል የኮሚሽኑን የመከላከል ሥራ መሠረት የሚገልጽ ሲሆን፤ ይህም ሕግ ከሚሰጠው አስገዳጅነት ባለፈ፣ በእያንዳንዱ ግለሰብ ውስጣዊ ማንነት ውስጥ የማይናጋ የታማኝነትና የኃላፊነት ግንብ በመገንባት የሀገርን ሀብትና ንብረት መጠበቅ ላይ ያተኩራል::

ሙስናና ብልሹ አሠራር የአንድን ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መዋቅር የሚያዳክም "ካንሰር" ነው:: ይህንን ካንሰር ለመከላከል ሕግና የቁጥጥር ተቋማት አስፈላጊ ቢሆኑም፣ ዘላቂ መፍትሔው ግን በእያንዳንዱ ዜጋ ልብ ውስጥ የሚገነባው ጠንካራ ሥነ-ምግባር ነው:: የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም ሥነ-ምግባርን እንደ ቀዳሚ "የግንብ አጥር" በመጠቀም፣ የዜጎችን ንቃተ-ሕሊና ለማሳደግና ግልጽነት የሰፈነበት አሠራርን ለመገንባት በቁርጠኝነት እየሠራ ይገኛል::

ይህ አባባል ጥልቅ የሆነ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ እና ግለሰባዊ ትርጉም አለው:: ሙስናና ብልሹ አሠራር በአንድ ሀገር ዕድገት፣ ፍትህ እና እኩልነት ላይ የሚጋረጥ ከፍተኛ አደጋ እንደመሆኑ መጠን፣ ይህንን አደጋ ለመከላከል ሕጎች እና የቁጥጥር ተቋማት ብቻቸውን በቂ አይደሉም:: እዚህ ላይ ነው ሥነ-ምግባር እንደ ዋናና የማይናጋ "የግንብ አጥር" ሆኖ የሚያገለግለው:: ይህ ሐሳብ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች ያጠቃልላል::

ውስጣዊ ቁጥጥር እና የሕሊና ዳኝነት፦ ሕግ የሚሠራው ጥፋት ከተፈጸመ በኋላ ወይም ጥፋት እንዳይፈጸም በውጭ አካላት ክትትል ሲደረግ ነው:: ሥነ-ምግባር ግን በሰው ልጅ ውስጣዊ ማንነት ውስጥ የሚገነባ የሕሊና አጥር ነው:: አንድ ግለሰብ ጠንካራ ሥነ-ምግባር ካለው፣ ማንም ባላየበት ወይም ሕግ በማይደርስበት ቦታ እንኳን ሳይቀር ከሙስና ይቆጠባል:: ይህም ሥነ-ምግባርን ከሕግ ይልቅ ጠንካራ እና ቀዳሚ መከላከያ ያደርገዋል::

የመከላከል አቅም (Preventive Power)፦ ሙስና ከመከሰቱ በፊት ቀድሞ መከላከል ከሁሉ የተሻለ አማራጭ ነው:: ሥነ-ምግባር ግለሰቦች ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን እንዲለዩ እና እንዲጸየፉ ያደርጋቸዋል:: ልክ እንደ ጠንካራ የግንብ አጥር፣ ሥነ-ምግባርም የስግብግብነት፣ የራስ ወዳድነት እና ያለአግባብ የመበልጸግ ስሜቶች ወደ ሥራው መስክ እንዳይገቡ ይገታል::

ተአማኒነትን እና ግልጽነትን መገንባት፦ በአንድ ተቋም ውስጥ ያሉ ሠራተኞች እና አመራሮች በሥነ-ምግባር የታነጹ ሲሆኑ፣ የተቋሙ አሠራር ግልጽ እና ተአማኒ ይሆናል:: ይህ ደግሞ ለሙስና ምቹ የሆኑ "ቀዳዳዎችን" ይደፍናል:: ሥነ-ምግባር ባለበት ቦታ አድልዎ፣ የዘመድ አዝማድ አሠራር እና ጉቦ ቦታ አይኖራቸውም::

ማህበራዊ ኃላፊነት እና ሀገራዊ ፍቅር፦ ሥነ-ምግባር የግል ጥቅምን ከመፈለግ ይልቅ የጋራ ጥቅምን ማስቀደምን ያስተምራል:: አንድ ግለሰብ ሙስናን ሲከላከል ሀገሩን እና ማህበረሰቡን እየጠበቀ መሆኑን ይረዳል:: ይህ አመለካከት ደግሞ ማህበረሰቡ ለሙስና ያለውን "ትዕግሥት መኖር የለበትም" (Zero Tolerance) እንዲያሳድግ ይረዳል:: በአጠቃላይ ሙስናን መዋጋት ማለት ውጤቱን ብቻ ሳይሆን መንስኤውንም ማከም ማለት ነው:: ሥነ-ምግባር በሌለበት ሁኔታ የሚወጡ ሕጎች እና የሚቋቋሙ የቁጥጥር ተቋማት ውጤታቸው ውስን ነው:: ሙስናን በዘላቂነት ለማጥፋት በየደረጃው ያለውን የሰው ኃይል በሥነ-ምግባር መገንባት የግድ ይላል:: ሥነ-ምግባር የሰውን ልጅ አስተሳሰብ እና ተግባር የሚገራ ጠንካራ "የግንብ አጥር" በመሆኑ፣ ይህንን አጥር ማጠናከር የትውልድ እና የሀገር ደህንነት ዋስትና ነው:: በመሆኑም ሥነ-ምግባርን እንደማይናጋ "የግንብ አጥር" በመጠቀም ሙስናን የመጸየፍ ባሕልን ማሳደግ የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል::



# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት እንዲሁም ሀገራችን ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻቸውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው:: በመሆኑም፣ በተከለከለ 'ፒራሚድ' የተሰኘ የሽያጭ ስልት ተጠቅመው ከ40 ሚሊየን ብር በላይ ለግል ጥቅም በማዋል የተከሰሱ ግለሰቦች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ልዩ ልዩ ወንጀል ችሎት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተላለፈባቸው:: ተከሳሾቹ ቲያንስ ኢትዮጵያ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ሚስተር ደዮንግ ጋንግ፣ አቶ ቴዎድሮስ በቀለ፣ ወ/ሮ ሱዓዳ ሙክታር የወንጀል ሕግ 34/1/1 የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 22/6/ እና 43/2/ ሥር የተደነገገውን የወንጀል ድርጊት በመፈጸም ዐቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦባቸው ነበር::

በዚህም ቲያንስ ኢትዮጵያ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአስመጪነት የንግድ ስራን ለመስራት የግብር ከፋይ መለያ ተመዝግቦ የአልሚ ምግብ አስመጪነት የንግድ ሥራ ፈቃድ በማውጣት ከ2004 እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያት ከውጭ ሀገር የሚያስመጣቸውን መድሐኒት እና የተለያዩ አልሚ ምግቦች ለመሸጥ ለሌሎች ተከሳሾች "የኮሚሽን ሽያጭ ወኪል በሚል ውል በመስጠት፣ በወኪሎች ስር እንዴት አባላት በሽያጭ ሰንሰለት ውስጥ እንደሚመለምሉ ስልጠና በመስጠት፤ የተለያዩ ግብይቱ የሚከናወንባቸውን ቅጾች በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ ተገቢ ያልሆነ የአባልነት ክፍያ እንዲፈጸም አድርጓል::

በድርጅቱ ስም የአባልነት መታወቂያ በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ፤ አባል ያልሆኑ አካላት ለግብይት የቀረቡ ምርቶችን እንዳይሸጥላቸው በማድረግ፤ አባል የሆኑት ደግሞ የተለያዩ ተከሳሹ ከውጭ ሀገር የሚያስገባቸውን ምርቶች አስቀድሞ ትዕዛዝ እንደተሰጠ በማስመሰል በስሙ በተመዘገበ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በቀጥታ በራሱና በወኪሎቹ አማካኝነት ከፍተኛ መጠን ያለዉ ገንዘብ በመሰብሰብ፤ በዚህም በአባልነት የተመዘገቡት ብዛት ያላቸው ግለሰቦች ወደ ሽያጭ ስልት ውስጥ አስገብቷል::

ለዚህም የተለያዩ ግለሰቦችን በመመልመልና በእነሱ ስር በሽያጭ ሰንሰለቱ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ብዛት ያላቸው ግለሰቦችን በሰንሰለቱ ውስጥ በማስገባት የተለያዩ አልሚ ምግቦችን እንዲገዙ ወይም የገንዘብ



መዋጮ እንዲያደርጉ እና በእነርሱ ቀጥሎ ሌሎች ሸማቾች የአልሚ ምግቦች የሚገዙ ወይም የገንዘብ መዋጮ የሚያደርጉ ከሆነ ወይም በሽያጭ ስልቱ የሚገቡ ከሆነ በሚገቡ ሸማቾች ቁጥር ልክ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ጉርሻ፤ የመኪና ሽልማት ወይም የውጭ ሀገር ጉዞዎች እንደሚያገኙ በማስመሰልና ሀሰተኛ ገለጻ በማድረግ፤ የአልሚ ምግቦቹን አሻሻጥ በመወሰን፤ ቅጾችን በማዘጋጀትና ስልጠናዎችን በመስጠት በአጠቃላይ የሽያጭ ስልቱን በመንደፍ በፈጸመው ፒራሚዳዊ የሽያጭ ስልት ተግባራዊ ማድረግ ወይም ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር ወንጀል ተከሷል::

በ2ኛ እና በ3ኛ ተከሳሾች ላይ በቀረበ 2ኛ ክስ ደግሞ ተከሸቹ ከጥር 2006 እስከ ጥር 2008 ዓ.ም ውስጥ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ-ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ከላይ በ1ኛ ክስ ውስጥ የተመለከተውን ተግባር 1ኛ ተከሳሽ እንዲፈጽም የመሩ በመሆናቸው በፈጸሙት ፒራሚዳዊ የሽያጭ ስልት ወንጀል ተከሰዋል:

በ3ኛ ክስ ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1 እና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀጽ 29/2/ለ እና መ ስር የተመለከተውን መተላለፉን ዐቃቤ ሕግ ገልጿል:: 1ኛ ተከሳሽ በ1ኛ ክስ ላይ በተመለከተው ወንጀል አማካኝነት ያገኘውን ገንዘብ ሕገ-ወጥ አመጣጡን ሰውሮ በስራ ላይ በማዋል፣ በማዘዋወር ወይም በባንክ በማስተላለፍ ህጋዊ አስመስሎ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 32 ሚሊየን 739 ሺ.ህ ብር እና በወጋገን ባንክ 7 ሚሊየን 768 ሺ.ህ ብር በድምሩ 40 ሚሊየን 507 ሺ.ህ 996 እንዲቀመጥ እና እንዲንቀሳቀስ በማድረግ ከወንጀል የተገኘ ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ተከሷል:: በ4ኛ ክስ በተመሳሳይ ቀሪ ተከሳሾች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ተከሰዋል::

የግራ ቀኙን ክርክር ያደመጠው ችሎቱ በ16 ተደራራቢ ክስ በተከሰሱት ተከሳሾች ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸውን በመግለጽ የጥፋተኝነት ውሳኔን በማሳለፍ፤ ለቅጣት ውሳኔ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል::

# መልካም ዜጋ

## በጎነት ለራስ ነው "የከተማ አውቶብስ ሹፌር" የመልካምነት ተምሳሌት!

በአዲስ አበባ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት የየካ ቅርንጫፍ የባስ ካፒቴን የሆኑት አቶ ብርሃኑ አየለ እና የአገልግሎት ክፍያ ተቀባይ አቶ ታምራት ተሾመ በአዲስ አበባ ከተማ አዉቶቡስ የጎን ቁጥር 1133 የጉዞ መስመር ከሜክሲኮ አባዶ የእለት ተግባራቸውን በመልካም ሥነምግባር እያገለገሉ ባሉበት ወቅት አቶ ሀይለማርያም የሚባሉ ተገልጋይ ይዘውት የነበረውን ላፕቶፕ ኮምፒዉተር ከነ ቻርጀሩ እንዲሁም መታወቂያና ዶክመንቶች ጥለው በመውረዳቸው ታማኝ አሽከርካሪ በክብር ለተቋማቸዉ አስረክበዋል::

ያስረከቡትን ሙሉ ንብረት መታወቂያዉ ላይ ባለ አድራሻ መሰረት የተቋሙ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ዳይሬክቶሬት አስፈላጊዉን



ማጣራት ካደረገ በኋላ ንብረት የጠፋባቸዉ ዐቃቤ ህግ አቶ ሃይለማርያምን ወደ ተቋሙ እንዲመጡ በማድረግ ለተቋማቸዉ ታማኝነት ሲሉ ንብረቱን ያገኙት ካፒቴን አቶ ብርሃኑ አየለ እና የአገልግሎት ክፍያ ተቀባይ አቶ ታምራት ተሾመ በዋናዉ መስሪያ ቤት በመገኘት የተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ኃላፊ አቶ ብርሃኑ አበበ ባሉበት ንብረቱን ለባለቤቱ አስረክበዋል::

የሰዉ ንብረት የሰዉ ነዉ ብለዉ ላደረጉት መልካምነት የአዲስ አበባ ከተማ አዉቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እያመሰገነ በቀጣይ መሰል ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የተቋሙ አግልጋዮች በሙሉ መልካም ተብብራችሁ ይቀጥል የሚል መልዕክት አስተላልፏል::

# ኪነ-ጥበብ

## ቃል...

አበው ሲተርቱ ከጥንት ከጥዋቱ፣
ቃል ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ ያሉት መሠረቱ::
በቢሆን አይደለም የወጉ ትርጉሙ የመሠረት ቅጡ፣
በቃል የተገባን በተግባር ሲገቡ እንዳይስቱ ጭብጡ::
በሹመት፣ በምርጫ፣ በቅጥር ቃል ሲጸፍ፣
በቃሉ መሠረት ከቃል ታች እንዳይሆን፣ ከልኩም እንዳያልፍ፤
ቃል ከሚጠፋ መሠራት አለበት ቃል እንዳይታጠፍ::
አበው እንደገሰጡን "ቃል ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ" ብለው በተረቱ፣
እኛም ተቀብለን ቃላትን በተግባር እንስራ በእውነቱ::
ሰው እውነትን ይዞ በእውነት ከሠራ፣
ሀቀኝነትና እምነት ይታያል ሲያበራ::
እውነት፣ ሀቀኝነት፣ እምነትን ሲፈጥሩ፣
ይነቀል የለም ወይ የሙስና ሥሩ::
የእውነት ምንጩ እምነት የሚያሳየው፣
ቃል ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ የሚለው ገዢ ነው::